هدية
HADIYAH

# የዑምራ አፈፃፀምና ህግጋት አጠርያለ ማብራሪያ

አማርኛ

أمهري



ምስጋና ሁሉ የአለማት ጌታ ለሆነው አላህ የተገባ ነው። ሶላትና ሰላም በነብያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ሁሉ ይስፈን።

**በመቀጠልም፦**

ይህ መልዕክት የነቢዩን መስጂድ የመዘየር ስነ ስርዓትና ህግጋትን አጠር ባለ መልኩ የሚያብራራ መልዕክት ነው። በዚህ መልዕክትም የነቢዩን መስጂድ የሚዘይር ሰው በአብዛኛው የሚያስፈልገውን ለማብራራት ጥረት አድርገናል።

አላህን ብቻ ለተከበረው ፊቱ ጥርት ተደርጎ የተዘጋጀ እንዲያደርግልንና ለመላው ሙስሊሙ ማህበረሰብ ጠቃሚ እንዲያደርግልን እንጠይቀዋለን።

**የእስላማዊ አስተምህሮቶችን በተለያዩ ቋንቋዎች አገልግሎት ማህበር የዕውቀት ዘርፍ ኮሚቴ**





# አጭር ማብራርያ
# የነቢዩን መስጂድ የመዘየር ስነ ስርዓትና ህግጋት





- የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) መስጂድ መዘየር ይወደዳል። የርሳቸውን መስጂድ ለመዘየር የተወሰነ ወቅት የለውም። ከሐጅ ተግባራት መካከልም አይደለም። ለሐጅ የሄዱ ሰዎች ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች የረሱልን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀብርም ሆነ የበቂዕን መቃብር ስፍራ የመዘየር ግዴታ የለባቸውም።

- የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀብር ለመዘየር አስቦ ጓዝን ሸክፎ መውጣትና መጓዝ አይፈቀድም። ቀብር ለመዘየር አምልኳዊ በሆነ መልኩ ጓዝን ሸክፎ መውጣት አይፈቀድምና። ጓዝን ሸክፎ (አምልኳዊ በሆነ መልኩ) መውጣት የሚፈቀደው ሶስቱ መስጂዶችን ለመዘየር ብቻ ነው። **ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል:** (ወደ ሶስት መስጂዶች ካልሆነ በቀር ጓዝን ሸክፋቹ አትጓዙ። (እነርሱም) ይህ መስጂዴ (መስጂደ ነበዊይ)፣ መስጂደል ሐራምና መስጂደል አቅሷ ናቸው።) ቡኻሪይ (1189) ላይ ሙስሊም (827) ላይ ዘግበውታል። ይህ የቃል አጠቃቀምም የሙስሊም ዘገባ ነው። ከመዲና የራቀ ሰው ቀብር መዘየርን በማሰብ ጓዝን ሸክፎ መውጣት አይፈቀድለትም። ነገር ግን የተከበረውን የነቢዩን መስጂድ መዘየር በማሰብ ጓዝ መሸከፍ ይደነገግለታል (ይፈቀድለታል)። መስጂዱ ዘንድ የደረሰ ጊዜም የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀብርና የባልደረቦቻቸውን ቀብር ይዘይራል። የርሳቸውን መቃብር መዘየር የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) መስጂድ መዘየርን ተከትሎ እግረ መንገድ ነው የሚዘየረው።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) አብዝተው ቀብር የሚጎበኙ ሴቶችን ስለረገሙ ሴት ልጅ የነቢዩንም (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሆነ የሌላን ሰው ቀብር መዘየር አይፈቀድላትም። ይህም እነርሱ ላይ ሙሾ ማውረድ፣ መገላለጥና ሌሎችም ሸሪዓን የሚፃረሩ ነገሮች ስለሚስተዋልባቸው ነው። ነገር ግን መስጂድ ውስጥም ሆነ ሌላ ሰፍራ ሆነው በአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ላይ ሶላትና ሰላም ማብዛት ይወደድላቸዋል። የትም ሰፍራ ሆና ሶላትና ሰላም ብትል (ሶለዋት ብታደርግ) ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይደርሳቸዋል። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሰላሉ ነው: (ቤቶቻችሁን መቃብር አታድርጉ። ቀብሬንም ዒድ (ቀን ተገድቦለት ተደጋግሞ የሚጎበኝ) አታድርጉት። በኔ ላይ ሶለዋት በሉ። የናንተ ሶላት የትም ብትሆኑ ትደርሰኛለች።) ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህም ብለዋል: (ለአላህ በምድር ውስጥ የሚዞሩ መላእክቶች አሉት። የኡመቴን ሰላምታ ያደርሱኛል።

هدية
HADIYAH

- ወደ ተከበረው የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) መስጂድ ሲገባ ቀኝ እግሩን ማስቀደሙ ይወደድለታል። የተቀሩት መስጂዶች ሲገባ እንደሚለውም (አልላሁምመፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲክ) ይበል። ትርጉሙም (አላህ ሆይ! የእዝነትህን በሮች ክፈትልኝ!) ማለት ነው።

- የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) መስጂድ ሲገባ የሚባል ሌላ የተለየ ዚክር የለም።

- ከዚያም የተሒየተል መስጂድ ሁለት ረከዓ ይስግዳል።

- ያለበት ወቅት ሶላት መስገድ የተከለከለበት ወቅት ካልሆነ በቀር የፈለገውን ያህል ሁለት ሁለት ረከዓ እያደረገ ሱና ሶላት መስገድ ይችላል። የአላህ መልክተኛ **(የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል:**
(በዚህ መስጂዴ የሚሰገድ ሶላት ከዚህ መስጂድ ውጪ ከሚሰገድ አንድ ሺህ ሶላት ይበልጣል። መስጂደል ሐራም ሲቀር።) ቡኻሪይ በቁጥር (1190)፣ ሙስሊም በቁጥር (1394) ዘግበውታል።






ከቻለ ረውዷ ዘንድ (እርሱም በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ሚንበርና በቤታቸው መካከል ያለ ሰፍራ ላይ) ለመሰገድ ጥረት ማድረግ ይገባዋል። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) እንዲህ ስላሉ ነው፡ (በቤቴና በሚንበሬ መካከል ከጀነት ጨፌዎች መካከል የሆነ ጨፌ አለ።) ቡኻሪይ በቁጥር (1195)፣ ሙስሊም በቁጥር (1390) ዘግበውታል። ረውዷ ዘንድ መሰገድ ለርሱ ካልገራለት መስጂድ ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ስፍራ ይስገድ። ይህ ግን የጀማዓ (የህብረት) ሶላት ካልሆነ ነው። የህብረት ሶላት ከሆነ ግን የመጀመሪያ ሶፍ መያዝን በማስመልከት የመጡ ጥቅል ማስረጃዎች ስላሉ ከኢማሙ ቀጥሎ ያለውን የመጀመሪያ ሶፍ ይዞ ይስገድ።

## የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀብርና የአቡበከርና ዑመርን ቀብሮች መዘየር የፈለገ ጊዜ:




የርሳቸው ቀብር (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ፊት ለፊት በሰርዓት፣ በአክብሮትና ድምፁን ዝግ በማድረግ ይቁም። ቀጥሎ በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ላይ (አሰላሙ ዐለይከ ያ ረሱሉሏህ ወረሕመቱሏሂ ወበረካቱሁ) በማለት ሰላምታን ያቅርብ። **(አሽሃዱ አንነከ ረሱሉሏሂ ሓቀን፣ ወአንነከ ቀድ በለግተ አርሪሳላህ፣ ወአደይተል አማና፣ ወጃሃድተ ፊላሂ ሐቀ ጂሃዲህ፣ ወነሶሕተል ኡምማህ፣ ፈጀዛከሏሁ ዐን ኡመቲከ አፍደለ ማ ጂዚየ ነቢየን ዐን ኡመቲህ)** የሚለውን ቢጨምርም ችግር የለውም። ትርጉሙም (እርሶ በእውነት መልክተኛ መሆኖትን፣ እርሶ መልዕክቶን እንዳስተላለፉ፣ አደራዎትን እንደተወጡ፣ በአላህ መንገድም ተገቢውን ትግል እንዳደረጉ፣ ለኡመቶ መካሪ እንደነበሩ እመሰክራለሁ። አላህ ሁሉንም ነቢያቶች ለኡመታቸው ባበረከቱት ነገር ከመነዳው የላቀውን ለኡመትዎ ላደረጉት ሁሉ አላህ ይመንዳዎት።) ማለት ነው።

ቀጥሎ ትንሽ ወደ ቀኝ አቅጣጫ ረመድ በማለት በአቡ በከር አስሲዲቅ (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና) ላይ ሰላምታን ያቅርብ።

ቀጥሎ በድጋሚ ጥቂት ወደ ቀኝ ከተጠጋ በኋላ በዑመር ቢን አልኸጧብ ላይ ሰላምታን ያቅርብ። ኢብኑ ዑመር (አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና) በረሱልና በሁለቱ ባልደረባዎቻቸው ላይ ሰላምታን ሲያቀርብ ብዙ ጊዜ (አሰሰላሙ ዐለይከ ያ ረሱለሏህ፣ አሰሰላሙ ዐለይከ ያ አባበክር፣ አሰሰላሙ ዐለይከ አባቴ ሆይ) ከሚለው ሰላምታ አይጨምርም ነበር።

የረሱል (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀብር ዘንድም ይሁን የአቡበከር ወይም የዑመር ቀብር ዘንድ ረጅም ሰዓት መቆም ወይም ዱዓ ማርዘም አይገባም። ኢማሙ ማሊክ ይህንን ያወግዙ ነበር። እንዲህም ብለዋል: **"ይህ ቀደምቶች ያልፈፀሙት አዲስ መጤ ነው። የዚህን ኡመት መጀመሪያ ያስተካከለው ነገር ካልሆነ በቀር የዚህን ኡመት መጨረሻ አያስተካክልም።"**

አንዳንድ ዘያሪዎች የሚፈፅሙት የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀብር ዘንድ ድምፅን ከፍ ማድረግና ረጅም ሰአት እዛ መቆም ይህ የተደነገገውን መቃረን ነው። የበላዩ አላህ እንዲህ ብሏል:

(يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تَرْفَعُوا أَصْوَاتَكُمْ فَوْقَ صَوْتِ النَّبِيِّ وَلَا تَجْهَرُوا لَهُ بِالْقَوْلِ كَجَهْرِ بَعْضِكُمْ لِبَعْضٍ أَنْ تَحْبَطَ أَعْمَالُكُمْ وَأَنْتُمْ لَا تَشْعُرُونَ ، إِنَّ الَّذِينَ يَغُضُّونَ أَصْوَاتَهُمْ عِنْدَ رَسُولِ اللَّهِ أُولَئِكَ الَّذِينَ امْتَحَنَ اللَّهُ قُلُوبَهُمْ لِلتَّقْوَىٰ لَهُمْ مَغْفِرَةٌ وَأَجْرٌ عَظِيمٌ)

(እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ድምጾቻችሁን ከነቢዩ ድምፅ በላይ ከፍ አታድርጉ። ከፊላችሁም ለከፊሉ እንደሚጮህ በንግግር ለርሱ አትጮኹ። እናንተ የማታውቁ ስትሆኑ ስራዎቻችሁ እንዳይበላሹ (ተከልከሉ)።

HADIYAH هدية

እነዚያ በአላህ መልክተኛ ዘንድ ድምጾቻቸውን ዝቅ የሚያደርጉ እነዚህ እነዚያ አላህ ልቦቻቸውን ለፍርሃት የፈተናቸው ነው። ለእነርሱም ምህረትና ታላቅ ምንዳ አላቸው።) [አልሑጁራት: 3- 2] የርሳቸው ቀብር ዘንድ ረጅም ሰአት መቆምና ሰላምታን በመደጋገም ማብዛቱ እርሳቸው ቀብር ዘንድ ወደ መገፋፋት፣ የጫጫታ መብዛትና የርሳቸው ቀብር ዘንድ ድምፅ ከፍ ማለትን ያስከትላል። ይህም አላህ ግልፅ በሆኑት የቁርአን አንቀጾች ለሙስሊሞች የደነገገውን ይቃረናል። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) በህይወት እያሉም ሆነ ሞተው የተከበሩ ናቸው። አማኝ ለሆነ ሰው ሸሪዓዊ ስነ ስርዓትን የሚፃረር ነገር ሊፈፅም አይገባውም።

ልክ እንደዚሁ አንዳንድ ዘያሪዎችና ሌሎችም ወደ ቀብራቸው በመዞር፣ እጆቻቸውን ከፍ በማድረግ ቀብራቸው ዘንድ ዱዓ የሚያደርጉ ይህ ሁሉ ከአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈን) ባልደረቦችና እነርሱን በመልካም የተከተሉት ቀደምት ደጋግ አበዎች ከነበሩበት ተቃራኒ ነው። ይልቁንም አዲስ ፈጠራ መጤ ነው።

ልክ እንደዚሁ አንዳንድ ዘያሪዎች በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ላይ ሰላምታን ሲያቀርቡ ልክ ሶላት የሚሰግድ ሰው እንደሚያደርገው ቀኝ እጃቸውን ግራ እጃቸው ላይ በማድረግ ከደረታቸው በላይ ወይም ከደረታቸው ስር ማድረግ ይህን ሁኔታ በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ላይ ሰላምታን ሲያቀርቡ መፈፀም አይፈቀድም። ምክንያቱም ኢብኑ ሐጀር ፈትሑልባሪ ውስጥ የተለያዩ ዑለሞችን ጠቅሰው እንዳወሱት ይህ አይነት ሁኔታ የመዋደቅ፣ የመተናነስና የአምልኮ ሁኔታ ስለሆነ ከአላህ ውጪ ለማንም አይሆንም።

هدية
HADIYAH

ለአንድም ሰው ድንጋይ በማበስ ወይም ቀብሩን ጦዋፍ በማድረግ ወደ አላህ መቃረብ አይፈቀድለትም። ረሱልን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጉዳዩን እንዲፈፅሙለት ወይም የታመመባቸውን እንዲፈውስላቸውና የመሳሰሉትን እንዳይጠይቅ። ይህ ሁሉ ከአላህ ብቻ ነው እንጂ ከሌላ ከማንም አይከጀልምና።

- መዲናን ለሚዘይር ሰው መዲና ባለበት ወቅት የቁባእን መስጂድ መዘየርና እዛ መስገዱ ይወደድለታል። ምክንያቱም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወደ ቁባእ መስጂድ እየጋለቡም በእግራቸውም እየመጡ ሁለት ረከዓ ይሰግዱበት ነበርና። ከሰህል ቢን ሐኒፍ እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: (ከቤቱ ጦሀራ አድርጎ (ዉዱእ አድርጎ) ከዚያም የቁባእ መስጂድ መጥቶ ሶላትን በውስጧ የሰገደ ለርሱ የዑምራ ምንዳ ይኖረዋል።)



ለወንዶች የበቂዕን መቃብር ስፍራ መዘየራቸው ሱና ነው። በቂዕ የመዲና መቃብር ስፍራ ነው። የሰማዕታት መቃብር ስፍራ ነው። የሐምዛ (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና) መቃብር ስፍራ ነው። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይዘይሯቸውና፣ ዱዓ ያደርጉላቸው ስለነበር ነው። እንዲሁም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሰላሉም ነው: (መቃብሮችን ከመዘየር ከልክያችሁ ነበር። መጪውን አለም ታስታውሳችኋለችና መቃብርን ዘይሩ።) እነርሱን ሲዘይርም ሌሎችን መቃብር ስፍራዎች ሲዘይር እንደሚለው ይላል: (አስሰላሙ ዐለይኩም አህሉድ-ዲያር ሚነልሙእሚኒነ፣ ወልሙስሊሚን፤ ወኢና ኢንሻአሏሁ ቢኩም ላሒቁን፤ ወየርሐሙሏሁ አልሙስተቅዲሚነ ሚና ወልሙስተእኺሪን፤ ነስአሉሏሁ ለና ወለኩም አልዐፊየህ) ይላል። ትርጉሙም (ከሙስሊሞችና ምእመናን የሆናችሁ የቀብር አለም ነዋሪዎች ሰላም በናንተ ላይ ይስፈን።አላህ ከሻ እኛ ወደናንተ መጪዎች ነን። ከኛ መካከል የቀደሙትንም የዘገዩትንም አላህ ይዘንላቸው። ለኛም ለናንተም አላህ ደህንነትን እንዲሰጠን እንጠይቀዋለን።) ማለት ነው።

ያለምንም ጥርጥር ቀብር በመዘየር የሚፈለገው መጪውን አለም ማስታወስ፣ ለሟቾቹ ዱዓ በማድረግ መልካም መዋል፣ **የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሱና መከተል ነው።** ሸሪዓዊ ይዘት ያለው ጉብኙት ይህ ነው።



ነገር ግን መቃብራቸው ዘንድ ዱዓ ለማድረግ በማሰብ መዘየር ወይም በነርሱ አማካኝነት ወይም በክብራቸው አማካኝነት አላህን ለመጠየቅና የመሳሰሉትን አላማ በማሰብ መዘየር ይህ የተወገዘ መጤ (ቢድዓዊ) የሆነ መዘየር ነው። አላህም ሆነ መልክተኛው (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) አልደነገጉትም። ደጋግ አበውም አልፈፀሙትም። ጉዳያችንን እንዲያስፈፅሙ ወይም የታመመን እንዲፈውሱና የመሳሰሉትን ሟቾችን መጠየቅ ግን ትልቁ ሺርክ ነው።



ውድ አንባቢ ሆይ! የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀብር በመዘየር ጉዳይ የተወሰኑ የተፈበረኩ ሐዲሦችን እንድታውቃቸውና በነዚህ ሐዲሦችም ከመሸወድ እንድትጠነቀቅ ከዚህ በታች እንዘረዝርልሃለን:

- የመጀመሪያ: (ሐጅ አድርጎ እኔን ያልዘየረኝ በርግጥም ችላ ብሎኛል።)
- ሁለተኛ: (ከሞትኩ በኋላ የዘየረኝ ሰው በህይወት እያለሁ እንደዘየረኝ ነው።)
- ሶስተኛ: (በአንድ አመት ውስጥ እኔንና አባቴን ኢብራሂምን የዘየረ ሰው ጀነት እንዲገባ አላህ ዘንድ ዋስትና እሆንለታለሁ።)
- አራተኛ: (ቀብሬን የዘየረ ሰው የኔ ምልጃ ለርሱ ፀንታለታለች።)

እነዚህና የመሳሰሉት ሐዲሦች አንዳቸውም ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) አልተረጋገጡም። ሓፊዝ አልዑቀይሊይ እንዲህ ብለዋል: "በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ አንድም ትክክለኛ የሆነ ሐዲሥ አልተላለፈም።" ሓፊዝ ኢብኑ ሐጀር ደሞ (ተልኺስ) በሚባለው መጽሐፋቸው ከነዚህ መካከል አብዛኛዎቹን ካወሱ በኋላ እንዲህ ብለዋል: "የነዚህ ሐዲሦች ሁሉም ሰነዶች ያልተረጋገጡ (ዶዒፎች) ናቸው።" ከሐጅ ወይም ከዑምራ በፊት ወይም በኋላ የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈን) መስጂድ መዘየር ከሐጅ ወይም ከዑምራ ሱናዎች መካከል ወይም ከማሟያዎች መካከልም የሚመደብ አይደለም። የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈን) መስጂድ መዘየር በጥቅሉ የሚወደድ ነው። አንድ ሐጅ ወይም ዑምራ አድራጊ የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈን) መስጂድ ካልዘየረ ወንጀል የለበትም። በሐጅና በዑምራ መካከልና የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈን) መስጂድ በመዘየር መካከል የሚያስተሳስራቸው ምንም ነገር የለም። የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈን) መስጂድ መዘየር እራሱን የቻለ አምልኮ ነው። ሐጅ ወይም ዑምራ ያደረገ ሰው የነቢዩን መስጂድ መዘየር አይጠበቅበትም። ልክ እንደዚሁ በተመሳሳይ የነቢዩን መስጂድ የዘየረ ሰውም ሐጅ ወይም ዑምራ ማድረግ አይጠበቅበትም። ሐጅንና ዑምራን የነቢዩን መስጂድ ከመዘየር ጋር አጣምሮ በአንድ ጉዞ ቢፈፅምም ችግር የለውም።

## የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) መስጂድ በሚዘየርበት ወቅት የሚስተዋሉ ስህተቶች:

-የመልክተኛውን (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) ቀብር በሚዘየርበት ወቅት በረከትን በመፈለግ ግድግዳዎችንና የቆሙ ብረቶችን (ፖሎችን) ማበስ፣ አጥሮቹ ላይ ገመዶችንና የመሳሰሉትን ማሰር፤
በረከት የሚፈለገው በአዲስ መጤ (በቢድዓ) ሳይሆን አላህና መልክተኛው (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሰፈንና) በደነገጉት መንገድ ነው።

ኡሑድ ተራራ ላይ ወደሚገኙ ዋሻዎች መሄድ፣ በተመሳሳይ መካ ውስጥ ወደሚገኙት ወደ ሒራ ዋሻና ወደ ሠውር ዋሻ መሄድ፣ እዛም ጨርቅ ማሰር፣ እዛም አላህ ያልፈቀደውን ዱዓ ማድረግና ለዚህም ብሎ ችግሮችን መጋፈጥ።

**እነዚህ የተጠቀሱት ባጠቃላይ ንፁህ በሆነው ሸሪዓ መሰረት የሌላቸው አዲስ መጤ ቢድዓ ናቸው።**



- የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ፋና አለባቸው ብለው የሚሞግቱትን ለምሳሌ ግመላቸው ያረፈችበትን ስፍራ፣ የኻቲምን ኩሬ ወይም የዑሥማንን ኩሬና የመሳሰሉትን አንዳንድ ስፍራዎች መዘየር፤ በረከትን ፍለጋም አፈርን ከነዚህ ስፍራዎች መውሰድ፤

- የበቂዕን መቃብር ስፍራንና የኡሑድ ሰማዕታት መቃብር ስፍራን በሚዘይርበት ወቅት ሟቾቹን መለመን፣ ወደ አላህ ለመቃረብና በሟቾቹ በረከትን ለማግኘት ብር ወደ መቃብሩ መወርወር፤

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ከትላልቅ ስህተቶች የሚመደብ ነው። ይልቁንም የእውቀት ባለቤቶች እንደጠቀሱት፣ የአላህ መጽሐፍና የመልክተኛው (የአላህ ሶላትና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሱና እንደሚያሳየው ከትላልቁ ሺርክ የሚመደብ ነው። አምልኮ ለአላህ ብቻ ነው የሚሰጠው ከአምልኮ መካከል ለምሳሌ ዱዓ፣ እርድ፣ ስለትና የመሳሰሉትን አንዳቸውንም ከአላህ ውጪ ለሆነ አካል መስጠት አይፈቀድም። ይህም አላህ እንዲህ ስላለ ነው:

(وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ)

"አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፤ ቀጥተኞች ሆነው ሊግገዙት እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ (ተለያዩ)" [አል-በይናህ፡ 5]

አላህ የበለጠ ዐዋቂ ነው! የአላህ ሰላትና ሰላም በነቢያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው ላይ ሁሉ ይስፈን።



HADIYAH
HAJI & MU'TAMR'S GIFT

هدية
هدية الحاج والمعتمر

www.hadiyah.org.sa